# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## <u>ዜና ዘገባ</u>

***መጋቢት 17 ቀን 2003 ዓ.ም.***

**የኦህዴድና የመለስ ፍጥጫ ተጋለጠ**

**ባለ ተራው የደኢህዴን ካድሬዎች ላይ ምንጠራ ተደረገ፤**

**የሰሜን አፍሪካው አመፅ ሊነሳ ነው በሚል የጅምላ እስራት ተጀመረ፤**

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ እና የኦህዴድ ፍጥጫና ትርምስ ምስጢሩ አፈትልኮ መውጣቱን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ጥቆማ አጋለጠ።

ከ20 ዓመት በላይ ስልጣን እርስቱ ያደረገው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ለቀጣይ አምስት አመት በድጋሚ አምና ተደረገ በተባለ ምርጫ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ የያዘ ቢሆንም በወቅቱ የኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቲ አባሎች በመቃወም ከፍተኛ ብጥብጥ ተከስቶ እንደነበር ያስታወሱት ምንጮቹ ይሄን ተከትሎ መለስ ግዜ ጠብቆ ሲያስተባብሩና ሲመሩ ነበር የተባሉትን የኦህዴድ ከፍተኛ ካድሬዎች ከአባዱላ ጀምሮ እስከ ታችኛው አመራር ድረስ ያሉትን እየተበቀለ መሆኑን ምንጮቹ አጋለጡ።

በቅርቡ የተጀመረው የኦህዴድ አመራር ምንጠራ እስከ ቀበሌ ድረስ ከመውረዱም በተጨማሪ በአባዱላ ግዜ የነበሩ ሁሉም አመራሮች ቀስ በቀስ እየተነሱ በአዳዲስ እየተተኩ መሆኑንም ምንጮቹ ገልፀዋል።

በኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቲ አባሎች በኩል መሪዎች በየአምስት አመቱ መለወጥ አለባቸው...... አባል ድርጅቶች የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ መያዝ አለባቸው..... በአንድ ግለሰብ ብቻ ከ20 ዓመት በላይ ስልጣን መያዝ የለበትም በማለት አዳማ (ናዝሬት) ላይ ተደርጎ በነበረው ጠቅላላ ጉባኤ

ጥያቄና ተቃውሞ ተነስቶ እንደነበርና ይህንኑ ለማርገብ ሲባል የኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቲን ለብቻ ሰብስበው በፌዴራል ፖሊስ አስከብበው በማስፈራራት በግዴታ እንዲቀበሉ የተደረገ ቢሆንም አሁን ግን ጊዜ ጠብቆ መለስ የቅጣት በትሩን እየዘረጋ መሆኑን ምንጮቹ ገልፀዋል።

በምርጫ ወቅት ኦህዴድ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ የማይረከብ ከሆነ አባዱላ ገመዳ ከኦሮሚያ ክልል ሬዝዳንትነት አይነሳም በማለት የክልሉ ምክር ቤት እና ማዕከላዊ ምክር አባሎች በሙሉ ድምፅ ወስነው የነበረ ቢሆንም ኩማ ደመቅሳ ...ሙክታር ከድር በተሰኙ የመለስ ተናጋሪ ሮቦቶች የተነሳው ጥያቄ ሁሉ ውድቅ ሆኖ መለስ በፈለገው መንገድ ተጉዞ ኦህዴድ አመራሮች እንዲበታተኑ እንደተደረገም ምንጮቹ አልሸሸጉም።

በወቅቱ የማዕከላዊ ብሎም የክልሉ ምክር ቤት አባሎችን ለማሳመን የተላኩት እነዚሁ የመለስ አሽከሮች «ይሄ አምስት አመት የስልጣን ዘመኑ ለመለስ የመጨረሻው ከመሆኑም በላይ በዚህ የመጨረሻ የስልጣን ዓመታት የትራንስፎርሜሽኑን እቅድ ከግብ ለመድረስ የጀመረውን እንዲጨርስ አንድ እድል ይሰጠው ...»በሚል ተማፅኖ ከማቅረባቸውም በላይ አባዱላ ከክልሉ ተነስቶ የቋም እስርኛ የሚሆንበት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተብየው ውስጥ አፈ ጉባዔ ሆኖ እንዲቀመጥ ማድረጋቸውን ምንጮቹ ወደ ሁላ መለስ ብለው ያስታውሳሉ።

በአሁኑ ሰዓት ዋና ዋና ናቸው የተባሉትን የኦህዴድ ከፍተኛ አመራሮች ከስልጣናቸው እያነሱ በየስርቻው እየመደቡዋቸው ሲሆን አባዱላንም ጠልፎ ለመጣልና እንደ ታምራት ላይኔ « ሲነገረኝ አልሰማ ብዬ ነው ስለዚህ ባጠፋሁት ጥፋት ቅጣት ይገባኛል » ብሎ በገዛ አንደበቱ እንዲናገር ሶስት የወያኔ ባለስልጣናት የተላኩ ቢሆንም ይሄ ሪፖርት እስከ ቀረበበት እለት ድረስ ያጠፋሁት ጥፋት የለም በማለት በአቋዋሙ ፀንቶ እንዳለም ምንጮቹ አጋልጠዋል።

ከብአዴን በረከት ስምኦን... ከደኢህዴን ሬድዋን ሁሴን..... ከኦህዴድ ሙክታር ከድር በመሆን ልክ እንደ ታምራት ላይኔ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ጥፋተኛ ነኝ ብሎ እንዲያምን ይህንንም በማድረጉ ምንም ችግር እንደማይደርስበት እያግባቡት ቢሆንም ሀሳባቸውን አልቀበልም ከማለቱም ባሻገር መውሰድ የሚገባችሁ እርምጃ ካለ በግልጽ ውሰዱ እንጂ እኔ ይሄንን በእኔ አንደበት አልናገረም በማለት ደፍሮ ምላሽ እንደሰጣቸው የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ አጋልጠዋል።

ስልጣን ያሰከረው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ አባዱላን አስለፍልፌ ......በህዝብ ዘንድ አዋርጄ ......የኦህዴዶችን አንገት አስደፍቼ በድል እወጣለሁ ብሎ ደረቱን ነፍቶ የነበረ ቢሆንም እንዳሰበው ያልሄደለት በመሆኑ ለግዜው በይደር ፋይል ውስጥ ተከትቶ አባዱላ በአይነ ቁራኛ እየታየ በደህንነት ሰዎች የቅርብ ክትትል እንዲደረግበት ተደርጎ እንደሚገኝም ምንጮቹ አስረድተዋል።

እንደ ፖለቲካ ተንታኞች እይታ ከሆነ የኦህዴድ ካድሬዎች ከአምስት ዓመት በፊት ጀምሮ በህዝብ ብዛት እና በቆዳ ስፋት አልፎ ተርፎ ለሀገሪቱ በገቢ ምንጭ ትልቅ ድርሻ ያለን እኛ ሆነን ሳለ ህወሀት ብቻ የመሪነት ቁልፍ ቦታዎችን መያዙ አግባብ አይደለም የሚል ጥያቄ እና ውዝግብ አንስተው ነበር ይላሉ ። ይሄ ሁኔታ አገርሽቶ መጥቶ ዛሬ ለህወሀቱ መለስ ዜናዊ የእራስ ምታት

ከመሆኑም በላይ ጀርባቸው አሁንም አልፀዳ ብሎ ስጋት ውስጥ እንዲገባ እና እንዲጠራጠራቸው አድርጎታል ብለዋል፡፡

ጉዳዩ ደግሞ ይላሉ እነኚሁ ተንታኞች አባዱላ የክልሉ ፕሬዝዳንት በነበረበት ወቅት ጠንክሮ ስር በመስደዱ የተደናገጠው መለስ ዜናዊ ከቦታው እንዲነሳና የካድሬዎቹ መረብ እንዲበጣጠስ እያደረገ ቢሆንም አሁንም ጨርሶ ሊያስወግደው እንደማይችል ተናግረዋል፡፡

ለዚህም ማሳያቸው በቅርቡ ከ120 በላይ የሙስና ታፔላ ተለጥፎባቸው የታሰሩት በሙሉ ከጥቂቶቹ በስተቀር የካቢኔ አባሎች ሲሆኑ ሌሎችም ከፍተኛ የተባሉት ባለስልጣናትን ከቦታቸው እያነሳ ወደ ዝቅተኛ ቦታ አስቀመጣቸው እንጂ ጨርሶ ሊያባርራቸው አልፈቀደም ፡፡ምክንያቱም አዲሱ የኦሮሚያ ፕሬዝዳንት ድጋፍ ስለሌለው በክልሉም ሆነ በኦህዴድ ውስጥ እጅግ አስቸጋሪ ነገር ሊፈጠር ስለሚችል አደጋውን በመፍራት መለስ ከዚህ የዘለለ እርምጃ ሊወስድ አይችልም ብለዋል፡፡

ይሁን እንጂ ይላሉ እነኚሁ ወገኖች መለስ በኦህዴድ ካድሬዎች ላይ የጀመረው ምንጠራ እና ሹም ሽር ይቆማል ማለት አይደለም ከበረሀ በመጣው ኩማ ደመቅሳና በአጎብዳጁ ሙክታር ከድር አማካኝነት ውስጥ ውስጡን ያልተማሩና ፊደል ያልቆጠሩ ሳይጠሩዋቸው አቤት ሳይልኩዋቸው ወዴት የሚሉትን እያሰባሰቡ ቦታ ቦታ መስጠታቸው አይቀርም..... ለዚህም ከወዲሁ ተጀምሮዋል ብለዋል፡፡

ባለፈው ሳምንት ውስጥ ሁለት የክልሉን ምክትል ፕሬዝዳንቶች ያነሳው መለስ በሙስና እንዳይከሳቸው መረጃ በማጣቱ ብቻ የአቅም ማነስ በሚል ወደ መምሪያ ውስጥ በትኖዋቸዋል ያሉት እነዚሁ ወገኖች ይሄም የሚያሳየው ቢሰናበቱ ለጠላት በር መክፈት መሆኑን አውቆ በስልጣናቸው ላይ ቢቀመጡ እንደማይተኙለት በመረዳቱ ነው ብለዋል፡፡

ከዚህ ቀደም ወዳጁ የነበረው አባዱላ እንኩዋን ተቀይሮ በመለስ ላይ መዶለቱን በመረዳቱ ቀጣይ ተሿሚ የክልል ፕሬዝዳንቶችን ስልጣን ለመቆራረጥ እና ለማሳነስ ባወጣው እቅድ መሰረት በአዲሱ አደረጃጀት ኦሮሚያ አራት ፤አማራ ሶስት፤ ትግራይ ሁለት ፤ደቡብ አራት ምክትል ፕሬዝዳንቶች እንዲሾሙ ተደርገዋል፡፡

እንዲህም ሆኖ በኦሮሚያ አዲስ ከተሾሙት አራቱ ምክትል ፕሬዝዳንቶች መሀከል የአባዱላ ቅርብና ምስጥረኞች ናቸው የተባሉት ሁለቱ ተነስተው በዝቅተኛ ቦታ እንዲቀመጡ ተደርገዋል፡፡

በተለይ ለመለስ ይቀርበዋል አዲሱን ፕሬዝዳንት ይቆጣጠረዋል ተብሎ ታማኝነቱ በነኩማ ደመቅሳ ተመስክሮለት የነበረው ዳባ ደበሌ የተባለው ምክትል ፕሬዝዳንት ጀርባው ሲጠና የመለስ ቀንደኛ ተፋላሚ ነው ተብሎ ድንገት ሳይታሰብ አሽቀንጥረው ወረውረውት የክልሉ የትምህርት ቢሮ ምክትል ሆኖ እንዲቀመጥ ተወስኖዋል፡፡

መለስ በራሱ ባለስልጣናት ላይ እምነት በማጣቱ የተነሳ አንዱን ሲሾም ሌላውን ሲሽር በየጊዜው እያመሳቸው መሆኑንም ከደቡብ የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል፡፡ ደራሽ ውሀ እንደሚያንገላታው ግንዲላ የኦህዴድ ባለስልጣናትን እያመሰና እያተራመሰ ባለበት በአሁኑ ወቅት ከሁሉም በላይ ታማኞቼ ናቸው

ብሎ ያስጠጋቸው የደኢህዴን ካድሬዎች ላይም የጥቃት ጦሩን ሰብቆ እየወረወረባቸው መሆኑ ታውቆዋል::

ግራ የተጋባውና መያዣ መጨበጫ ያጣው መለስ ዜናዊ ከኦህዴድ ባለስልጣናት ቀጥሎ ሰሞኑን ደግሞ ደኢህዴን በተባሉት ተላላኪ አሽከሮቹ ላይ ሹም ሽረት ማድረግ የጀመረ ሲሆን በተለይ አዲስ አበባ ውስጥ በታማኝነታቸው ተመርጠው ተቀመጠው የነበሩ ደቡቦች በሙሉ ነስተው በህወሀት እና በብአዴን መተካታቸው ታውቆዋል::

ኦሮሚያን ሲያምስና ሲያተራምስ የሰነበተው የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ኩማ ደመቅሳ ፊቱን መለስ አድርጎ በአዲስ አበባ ውስጥም የምንጠራ ዘመቻ የጀመረ ሲሆን ሰሞኑን በደኢህዴን ካድሬዎች ላይ ዘመቻው ተጠናክሮ መቀጠሉን የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

ታማኝ ናቸው ተብሎ ከቀበሌ እስከ ከተማው ምክር ቤት ድረስ ተሾመው የነበሩት እነዚሁ የደኢህዴን ካድሬዎች ላይ የጥቃት በትሩን እያሳረፈባቸው ያለው የመለስ ቀኝ እጅ እንደሆነ የሚነገርለት ኩማ ደመቅሳ ካድሬዎቹን በወንጀል እየከሰሰ ዘብጥያ እያወረዳቸው መሆኑንም ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል::

እስከ አሁን ድረስ ቦታው ላይ ሆነው በህዝብና በሀገር ላይ ሲቀልዱና ሲጫወቱ የነበሩትን እነዚሁ ባለስልጣናት ወያኔ ሲያሞካሽና ሲያወድስ እንዳልነበረ ዛሬ ድንገት ከመለስ በተሰጠ የምንጠራ ዘመቻ ከያሉበት እየተነሱ ከስራ ሲባረሩ ገሚሶቹ ክስ ተመስርቶባቸው ዘብጥያ እየወረዱ መሆኑንም አጋልጠዋል::

በተባረሩት የሁለቱ ተለጣፊ ድርጅት ባለስልጣናት ምትክ የህወሀትና የብአዴን ካድሬዎች ቦታውን እንዲረከቡ እየተደረገ ከመሆኑም በላይ አፍላ ፍቅር ውስጥ ገብተው ለማን ይድላው በሚል ቀድሞ ተባረሩ የተባሉት በረሀ አመጣሾች ሁሉ እየተሰገሰጉ መሆኑ መለስ ከበረሀ የመጡት ካድሬዎች በችግር ግዜ ጥለው አይጥሉኝም የሚል ግምት መያዙን የሚያመላክት መሆኑን ያሳያል ተብሎዋል::

በተለይ ሌሎቹ የወያኔ ተለጣፊ ድርጅት ካድሬዎች ከቦታቸው ሲነሱ እድለኛ ከሆኑ ከነጭራሹ ይባረራሉ አለበለዚያ ሰበብ ተፈጥሮላቸው ወደ እስር ቤት ሲገቡ የህወሀት ካድሬዎች ግን ከአንደኛው መስሪያ ቤት ተነስተው ወደ ሌላኛው በእድገት ሲዛወሩ አለበለዚያ በተመጣጣኝ ቦታ እንዲቀመጡ ይደረጋሉ::

በመስከረም ወር ተደረገ በተባለ ለውጥ ላይ የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽነር የነበረው ወዲ ሻምበል ከአራት ከፍተኛ አመራሮች ጋር ተነስቶ በጡረታ ተሰናበተ ሲባል የቤተ መንግስት ዙሪያ ጥበቃ የደህንነት ኃላፊ ሆኖ የተሾመ ሲሆን ሌሎቹም በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ከፍተኛ ስልጣን ተሰጥቶዋቸው ተቀምጠዋል::ሌላው ቢቀር የትግራይ ክልል ርዕሰ መስተዳድር የነበረው ጸጋዬ በርሄ በጡረታ ተሰናበተ ተብሎ ሲናፈስ ቢቆይም የፌዴራል ደህንነት ዋና አማካሪ ሆኖ ቁልፍ ስልጣን እንዲይዝ ተደርጎ ተሾሞዋል::

መለስ እጅግ ግራ ከመጋባቱ የተነሳ የሚይዘውና የሚጨብጠውም ስለጠፋው የአምስት ዓመቱን እድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ክለሳ በሚል ለሁለት ወር የሚቆይ ስልጠና እንዲሰጣቸው አድርጎ ባለስልጣናቱን ከርችሞ ይዞዋቸዋል::ይህንንም ያደረገበት ዋነኛ ምክንያት የነበረውን ውጥረት ለማለዝብ አስቦ ሳይሆን እንዳልቀረም ይገመታል::

በሌላ ዜና የወያኔ ቡድን ባደረበት ፍርሀት እና ስጋት የተነሳ የተቃዋሚ ፓርቲ አባሎችን የሰሜን አፍሪካው የህዝብ አመፅ ሀገር ውስጥም መከሰት አለበት እያላችሁ ህዝቡን እየቀሰቀሳችሁ ነው በማለት በጅምላ እስር እያካሄደ መሆኑን ከተለያዩ ቦታዎች የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

ቱኒዚያ..... ሊቢያና ግብፅ ብሎም አረብ ሀገራት እንደተከሰተው የህዝብ አመፅ ሁሉ በእኛም ሀገር ህዝቡ አመፅ እንዲያነሳና ሁከት እንዲከሰት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እየቀሰቀሳችሁ ነው በሚል የወያኔ ቡድን ከፍተኛ ባለስልጣናት ሰሞኑን በተለያዩ ከተሞች ውስጥ የተቃዋሚ ፓርቲ አባሎችን ብሎም ዜጎችን ከየቦታው እያፈሱ ለእስር እየዳረጉ መሆኑ ተገለፀ::

በነቀምት ...በደምቢዶሎ...በአምቦ....... በባሌ .....በአርሲ እና በናዝሬት ከተሞች ውስጥ ህዝቡን አመጽ እንዲያነሳ ሲቀሰቅሱ ነበር የተባሉ ከ200 በላይ ዜጎች ከየቤታቸው፤ ከሚሰሩበት ቦታና ከየመንገዱ ላይ በደህንነቶች ታፍነው እየተወሰዱ መሆኑን ያጋለጠው የኦሮሞ ህዝብ ኮንግሬስ(ኦህኮ) እስከ አሁን ቁጥራቸው ያልታወቀ ዜጎች የጅምላ እስር እንደተፈጸመባቸው አጋልጦዋል::

የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግሬስ (ኦብኮ) የተሰኘው ፓርቲ እንደገለፀው ከሆነ በኢትዮጵያም ውስጥ በተለይ በኦሮሚያ ክልል የህዝብ አመጽ እንዲከሰት እየተንቀሳቀሳችሁ ነው በሚል ተራና ተልካሻ ምክንያት ዜጎች ከየጎዳናው ላይ እየታፈሱ ለእስር ከመዳረጋቸውም በተጨማሪ የት እንደሚወሰዱ እንደማይታወቅ የገለፀ ሲሆን ቤተሰቦቻቸው ያሉበትን ባለማወቃቸው ተቸግረው በከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ እንዳሉም አብራርቶዋል::

ህዝቡ በኑሮ ውድነት ከፍተኛ ችግር ውስጥ ወድቆ ባለበት በዚህ አንገብጋቢ ወቅት የወያኔ ቡድን የነዳጅ ዋጋ ጨምሮ የበለጠ ችግሩ እንዲባባስ ከማድረጉም ባሻገር በሀገር ውስጥ የሚመረቱትን ስኳር .....ቡና እና ሌሎች መሰል ነገሮች ከገበያ እንዲጠፉ አድርጎ በህዝቡ ስቃይ ላይ እየቀለደ ቢሆንም ውስጣዊ ፍርሀቱ እያየለና እየሰፋ በመምጣቱ የተነሳ ህዝቡን ለማፈንና ለመጨፍለቅ ሲል አመፅ እንዲነሳ እየቀሰቀሳችሁ ነው በሚል የጅምላ እስራት መፈፀሙ አሳፋሪና አሳዛኝ ነው ሲል ህዝቡ ውስጥ ውስጡን ቁጣውን እየገለፀ ይገኛል::

የወያኔ የግፍ አገዛዝ የሰለቸውና የተማረረው ህዝብ አንዱ በፖለቲካ አመለካከቱ ሌላ ግዜ በኑሮ ውድነት ባሰማው ብሶት በደህንነት እና በፌዴራል ፖሊስ እየተንገላታ እና እየተሰቃየ በገዛ ሀገሩ እንደ ባዕድ ተቆጥሮ ሲታሰር ሲፈታ ለ20 ዓመታት የቆየ ቢሆንም አሁን የግፉ መጨረሻ ላይ መድረሱን የተገነዘቡት ወያኔዎች ውስጣቸው በተፈጠረ ፍርሀት ምክንያት ከወዲሁ ችግሩን ለማፈን ሲሉ ህዝቡን እያመሱት ቢገኙም ቀኑ ሲደርስ መፈንዳቱ አይቀሬ መሆኑን ህዝቡ እያጉረመረመ መሆኑ ታውቆዋል::

በተለይ በአሁኑ ሰዓት ወያኔ ከነጋዴው ጋር በጀመረው እሰጥ አገባ የተነሳ የከረረ ጥላቻ ውስጥ ከመግባቱም በላይ የሚያወጣውን መመሪያና ትዕዛዝ የሚያከበረው ጠፍቶ በሁለቱ ቡድኖች መሀከል ውጥረት ነግሶዋል::

ከአፍሪካ በግዙፍነቱ የሚታወቀው የመርካቶ ገበያ ወያኔ በፈጠረው የተዛባ አመለካከት እና በተፀናወተው የዘረኝነት አባዜው ከነጋዴው ጋር ሊግባባ ባለመቻሉ የንግዱ እንቅስቃሴ እንዲዳከም ከማድረጉም በላይ ያወጣው መመሪያና ደንብ ጨርሶ እየተናደ እና ነጋዴውም በወያኔ ላይ ንቀት እያሳረፈ መምጣቱ ታውቆዋል::

ከነገ ዛሬ የህዝብ አመፅ ድንገት ሊገነፍል ይችላል ብሎ በፍርሀት ማዕበል ውስጥ እየተናጠ የሚገኘው የወያኔ ቡድን በኦሮሚያ ችግሩን ለማርገብ በሚል የጅምላ እስራት እየፈጸመ ሲሆን ከታሰሩት መሀከልም ብዙዎቹ ነጋዴዎች መሆናቸው የስጋት አቅጣጫው የነጋዴው ህብረተሰብ መሆኑን የሚያመላክት ሆኖ ተገኝቶዋል::

የወያኔ ቡድን ከዚህ ቀደም እንደሚያደርገው ነጋዴዎቹን በቁጣና በማስፈራራት መያዝ እንደማይቻል በመረዳቱ በልምምጥና በስብሰባ ለመያዝ ቢሞክርም ሆዱ የሻከረው ይሄው የንግዱ ህብረተሰብ ፊት ነስቶት አልፎ ተርፎ ከወያኔ ጋር ቆርጦ ለመፋለም እየተዘጋጀ ባለበት ሰዓት አዲስ አበባን ትቶ በክልል ከተሞች ያለውን ጫና ለማብረድ መነሳቱ የቱንም ያህል ዜጎችን እያፈሰ ቢከትም ህዝቡ በወያኔ እጅግ ስለተማረረ አመፁ አይቀሬ ነው ሲሉ ነጋዴዎች በይፋ እየተናገሩ ይገኛሉ::

ዛሬ አንድ ኪሎ ስኩዋር ለመግዛት በአስር ከሎ ሜትሮች ከመኖሪያው ርቆ የወጣው ህዝብ በሰልፍ ቀኑን ሙሉ ውሎ አልቆዋል እየተባለ ባዶ እጁን እየተመለሰ ባለበት እና በአንጻሩ የወያኔ ቡድን ወደ ውጭ ሀገር እየላከ በሚያገኘው ገንዘብ የጦር መሳሪያ እየገዛ መልሶ ሊያፍነው መሆኑን የተገነዘበው ህዝቡ በወያኔ ላይ የማያዳግም እርምጃ ከመውሰድ ወደ ሁዋላ እንደማይል የተረዳው ዘረኛው ቡድን በየቦታው በምስጢር ጦር እየሰገሰገ መሆኑንም ከተለያዩ ከተሞች የደረሱን ጥቆማዎች ገልጸዋል::

በአዲስአበባ፤በጅማ፤በሐረር፤በደሴ፤በነቀምት፤በባህርዳር፤በደብረማርቆስ፤በአምቦ በፍቼ እና በሌሎችም ከተሞች የጦር ሰራዊቱን በምስጢር በየካምፖቹ እና መጋዘኖች ውስጥ ሰግስጎ እየተጠባበቀ ያለው የወያኔ ቡድን ህዝቡ እርምጃ እንደሚወስድበት አስቀድሞ ስላወቀ የለመደውን አረመኔያዊ እርምጃ ለመውሰድ እየተዘጋጀ መሆኑም ታውቆዋል::

ወትሮ በግርግሩ የሚታወቀው ምንም ተጠይቆ የማይጠፋበት የመርካቶ ገበያ ዛሬ ቀዝቅዞ አለ ከሚባለው ይልቅ አልቆዋል የሚለው ቃል በነገሰበት ሰዓት መልሶ ነጋዴውን ለመጨፍለቅ ሌት ከቀን እየተራወጠ የሚገኘው ወያኔ ሰሞኑን ስብሰባ በተደጋጋሚ ቢጠራም አንድም ነጋዴው ሳይገኝ በመቅረቱ የበለጠ ስጋት ላይ ሊወድቅ እንደቻለም ለማወቅ ተችሎዋል::

ጭር ሲል አልወድም የሚለው ዘረኛው የወያኔ ቡድን መጪው የፋሲካ በዓል በሰላም እንዳያልፍ በመፈለጉ እጅግ ቁጥሩ የበዛ የከተማ ውጊያ ሲለማመድ የነበረ ጦር በየከተማው በትኖ ህዝቡን እያስፈራራ እንደሚገኝም ከተለያዩ ከተሞች የደረሰን ጥቆማ አጋልጠዋል::